# <u>የሐሰት ዜና ቀለብና አጉል ተስፋ ጥረቃ</u>

ሙሉጌታ ደረጀ

በፖለቲካ ትግል ሆነ በመንግሥታት ፉክክር ደረጃ የሐሰት ዜና ማሰራጨት ዘዴ በስራ የሚውል ነው። ጥቁር ፕሮፓጋንዳ ይሉታል። የሐሰት ዜና አሰራጭቶ ጠላትን ማደናገር ነው ዓላማው። በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ጊዜ ጀርመንም እንግሊዝም በሰፊው ተጠቅመውበታል። ወያኔ በበኩሉ 03 የሚል የሀሰት ዜና የሚያሰራጭ ክፍል ነበረው። ሕዝብን የሚያደናግር የፈጠራ ዜና ና የሀሰት መረጃ የሚያሰራጭ ማለት ነው።

በአሁኑ ጊዜ አንዳንድ ተስፈኞችና አወናባጅ ወያኔዎች የሱዳኑ በሺር ለፍርድ ይቅረብ በመባሉ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊም " ደንግጧል" ፤ " ለፍርድ ሊቀርብ ነው" ወዘተ በሚል እየጮሁ ናቸው። ይህ አጉል ተስፋና ጭራሽም መሰረተ ቢስ ዜና ነው። መለስ ዜናዊ የዋሽንግተን ሎሌ ነውና የሚነካው የለም። ለምን በሺር ተከሰስ ብሎ ቢጮህ ለራሱ ሰግቶ ሳይሆን የሱዳኑን በሺር በጎኑ ለመያዝ ነው። ታዲያ የዋህ አይሏቸው ጅል ሀበሾች ደግሞ መለስ በዚሁ አሜሪካና እንግሊ ዝ በሚያሽከረክሩት ፍርድ ቤት መለስ ሲከሰስ ይታያቸዋል። ወያኔ ስልጣን የያዘ ጊዜ መንግስቱ ኃይለ ማርያም ጥቁር አንበሳ የሚል ጦር ይዞ በጋሞጎፋ መጣ ሲባል የነበረው ዓይነት ነው። በዘመነ ደርግ ኢዲኅ ታንክ በግመል ጭኖ ሲመጣም ሰምተን ነበር። ብርሃኑ ነጋም ጦር አውጆ ሊዘምት ሲያንራ ጊዜ አለፈ ። አጉል ወሬ፤ባዶ ተስፋ። ሕዝብን ማዘናጊያ። ማስተኛ። ሕዝብ በራሱ ጥረትና ትግል ላይ እንዳያተኩር ለማድረግና በአጉል ተስፋ ስርየት ይመጣል ብሎ እንዲጠ ብቅ ለማድረግ ማለት ነው። ወያኔ ከሻቢያ ጦርነት ሲገባ አሰብን ላስመልስ ነው የሚል የሀሰት ዜና ረጭቶ ነበር። ያሙነትም ብዙ ነበሩ። መለስ ዜናዊ በምዕራቡ ታቅፎ እያለ እንደ በሺር ሊከሰስ ነው ብሎ መለፈፍ ጅልነትና ሕዝብንም ማደናገር ነው።

በሀሰት ዜና ቀለብ የሚጠግቡና አጉል ተስፋን አቅፈው እሹረሩ የሚሉ ለሀገር አይጠቅሙም። ሀገር ልትጠፋ ምጥ ተይዛ ባለችበት ጅልነት የሚፈቀድ ቅንጦት ሊሆን አይችልም። ነጋ ጠባ መታለልና ለሀገር አጥፊዎች ሰለባ መሆን አይበጅም። ከዚህ ቀደም ወያኔ ራሱን ኢሕአዴግ ሲል ኢትዮጵያዊ ሆነ ብለው የተሞኙ ነበሩ። ለስልጣን ሲበቃም ልጆቼ ብለው ያቀፉት እነ ፕሮፌሰር መስፍን ዛሬም በመድረክ ሲጮሁ እየሰማን ነው። ቆይቶም ለሻዕቢያና ኦነግ መሳሪያ የሚሆን ተቋም/ ትብብር ለነፃነትናዴሞክራሲ ወይም ኤ ኤፍ ዲ የተባለው/ ሲቋቋም ወያኔ አበቃለት ብለው የቧረቁ የዋሆች ጥቂት አልነበሩም። ዛሬ ደግሞ ከመለስ ባልተናነሰ የከፉ ጠባቦች ለሀገር ቆመዋል ብለው ሊያሳምኑን የሚጥሩትን እያየን ነው። ከነ ገብሩ አስራትና ስዬ ጋር እንኩልኩል የሚሉት ሁሉ ጅሎች ናቸው ብሎ ማለፍ አይቻልም። ቀቢፀ ተስፋ ያጠቃቸው ግለሰቦች ላም አለኝ በሰማይ ሆኖባቸው ያለፈው ያገደመው ሁሉ ነፃነት ሊያመጣ ነው ብለው ቢወናበዱ እምብዛ ም ላንገረም እንችላለን። ገብሩ አሥራት ና ስዬ ብለው ኡ ኡ የሚሉት አንጃዎችና ባንዳዎች

ግን ተጃጅለው ሳይሆን ሀገራቸውን ሽጠው ነው። መድረክ የተባለው ስብስብ የጠባቦች ስብስብ መሆኑን አዛውንቱ ቡልቻ ደመቅሳ በራዲዮ ቃለ መጠይቅ ግልፅ አድርገውልናል። ምን አሉ? በመድረክ የሚገባ ማንኛውም ድርጅት በቅድሚያ በካፒታሊዝምና ለጥቆም በብሄረሰብ ፌዴራሊ ዝም/ክልል/አንቀፅ 39/ ማመን አለበት አሉ። ኢትዮጵያን ሊበታትናት ነው ብለን በምንቃወመው የወያኔ ፖለቲካና ፖለሲ ማመን ወሳኝ ነው ብለዋል አቶ ቡልቻ። አቶ ቡልቻ በስተርጅና ጡረታ ሲወጡ ፖለቲካን እንደ የጡረታ ጉዳይ ወይም ጊዜ ማሳለፊያ ይዘው በመነሳታቸው ይህን ያህል ም የፖለቲካ ዕውቀት የላቸውም በሚል ይቅርታ ሊደረግላቸው ቢችልም የመድረክ ስብስብን አቅዋም ግን ግልፅ አድርገዋል። ገብሩ አሥራትና ስዬ አብርሃ ከመለስ ባልተናነሰ ፀረ ኢትዮጵያ ጠባብ ብሄረተኞችና የትግራይ ትምክህተኞች ናቸው። ላደረሱት በደል እስካሁን ይቅርታ አልጠ የቁም። ያለፈውን አታንሱብን ከማለት ሌላ። ሌላው ቢቀር ግን የኢሕአፓ አባሎች ነበርን የሚሉ ይ የዛሬ አንጃዎች እንዴት ጓዶቻቸውን ያጠፉትን እነ ገበሩና ስዬን ወዳጅ አጋር ብለው ሊናገሩ ተነሱ ማለታችን አልቀረም። ለዝቅጠትና ክህደት መቆሚያ ገደብ የለውም ማለት ነው? ሰፊ ህብረትና መድረክ በሚል ጭምብል እየተገፋ ያለው አሳፋሪ ፖለቲካ መስመር ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶችና የወያኔን ስርዓት ሊቀጥሉ ከሚመኙ ከህዲዎች ጋር መሰለፍ ነው። የመድረክና የነስዬ አቅዋም አቶ ቡልቻ እንደገለፁት የብሄረሰብ ፌደራሊዝም ማለትም የክልልና የጎጠኝነት ፖለቲካ ነው። ከፋፋይና ሀገር አጥፊ። ይህን ያልተቀበለ የመድረኩ አባል ሊሆን አለመቻሉን አቶ ቡልቻ ገልጠዋል። እነ ገብሩና ስዬ ደግሞ ቢያንስ የአረና መርሐ ግብር አንቀፅ 39ን የሚቀበልና በመሰረቱ የህወሓትን ፖለቲካ የሚገፋ መሆኑን ነግረውናል። ታዲያ ከመለስ ጋር የግል የስልጣን እንጂ የመርህ ልዩነት ከሌላቸው ጋር ለመተቃቀፍ የአንጃዎች ጫጫታና ሩጫ ክህደትና ውርደት እንጂ ሌላ ምን ሊባል ይቻላል?

ስዬ ገብሩና አረና አዲስ ክስተት ናቸው፤ የወያኔን ብቸኛ ስልጣን አስተነፈሱ ሊሉን የተነሱት ሁሉ የሀሰት ዜና ሰለባዎችና የአጉል ተስፋ አራጋቢዎች ናቸው። ለአደናጋሪ ፕሮፓጋንዳ ተጠቂ መሆን ማቆም አለብን። ወያኔ የሀሰት ዜና ሲነዛ በዚያው ተቃኝቶ መንጎድ ተገቢ አይደለም። መጃጃልና ሀገርን መጉዳት ይከለተላል። ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ሰማይ ከምድር ቢገጥምም የነ ገብሩ አሥራት አረና ሆነ የነስዬ መድረክ ለኢትዮጵያ ቅንጣት የሚበጅ ሳይሆን ያከተመለትን የመለስ-ስብሀትን ዘረኛ አገዛዝ ዕድሜ በአዲስ መልክ ለመቀጠል የተቃኘ ነው። መድረክ በገብሩ አሥራት አመራር ዋና ዓላማው ሊወድቅ ያለው የመለስ አገዛዝ የትግራይን የበላይነት እንዳያስጠ ቃ ሊያድስ ሊከላከል የቆመ ነው። እነ ገብሩና መለስ ለምን ሕዝብን ይቅርታ አይጠይቁም የሚለ ው እንዳለ ሆኖ ግለሰቦቹና ስብስባቸው አገዛዙን በአዲስ መልክ ሊቀጥሉ መነሳታቸው ነው ዋናው ችግር። የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔ ከነስርዓቱ እንዲወድም ይፈልጋል። እነ ሰዬና ገብሩ ደግሞ መለስ ተወግዶ ወይ ቦታ ለቆ የወያኔ የበላይነት እንዲቀጥል ይፈልጋሉ። እነ ከህደቱና በየነ ጴጥሮስም ቢሆኑ ይህን ማጅብ ፈላጊ ናቸው። አንጃዎች ከዚህ ስብስብ ጋር ሊለጠፉ ቢፈልጉም እስካሁን ያለው መረጃ እነ በየነም ሆኑ ገብሩ የአንጃን መምጣት ፈላጊ አይደሉም። አጉል ምኞት

ይሏል ይህ ነው፡፡ አንጃው ግን በራሱ መስመር ከወያኔ ጋር በፀጥታው ሀላፊ በጌታቸው አማካኝነ
ት አስገቡን ንግግር--ልምምጥ መጀመሩ ደግሞ የከረመ መሆኑ ተጋልጧል፡፡ዳግም አጉል ተስፉ፡፡

የሐሰት ዜና ቀለብ ወደሚለው ስንመለስ የኦባማ አስተዳደር ወያኔን ያስጨንቀዋል ብለው የሚለ
ፍፉትም ሌሎች አደናጋሪና የአጉል ተስፋ ሱቅ በደረቴዎች ናቸው፡፡ የአሜሪካው አስተዳደር ዋና
ዋና ባለስልጣናት ከማዳም ክሊንተን እስከ ሱዛና ራይስ የመለስ ወዳጆች ናቸው፡፡ መለስ ለአሜሪካ
ያደረ መጋዣ በመሆኑ ቡሽ ተባለ ኦባማ ወግድ የሚሉት አይደለም፡፡ ታማኝ  ውሻን ከቤቱ
የሚያባርር አለ ? ስለዚህ የአሜሪካ ፖሊሲ ይለወጣል፤መለስ ለዓለም አቀፍ ፍርድ ይቀርባል፤ እነ
ስዬና ገብሩ የትግራይ ጠባብነተቻውን ትተው ኢትዮጵያዊና ዴሞክራሲያዊ ይሆናሉ ብለው
ሊያሞኙን የሚጥሩትን ሁሉ  ፃኡ ንዑሰ ክርስቲያን ከአፀደ መቅድሱ እንደተባለው ወግዱ አወናባ
ጆች፤ከሀዲዎችና አንጃዎች ብለን ልናሳፍራቸው ይገባል፡፡
የሐሰት ዜና ቀለብ የተራበን ሆድ አይሞላም፡፡ የአጉል ተሰፋ ጥረቃም ፋይዳ ቢስ ነው፡፡ ወያኔ
ፀረ ሕዝብ ነው፡፡  ወያኔን በአዲስ መልክ ሊያስቀጥሉ የሚሞክሩ አረና--መድረኮችም የሕዝብ
ወገን አይደሉም፡፡ እነዚህን የሚደግፉ አንጃዎችና ሌሎችም ሰልፋቸው ወያኔያዊ እንጂ ሕዘባዊ
አይደለም፡፡ ሀቁ ይህ ነው፡፡ ስዬና ገብሩ፤ በየነና ቡልቻ የወያኔ ዘረኛ ስርዓት መቀጠሉን ፈላጊ
ናቸው፡፡ ተጠቃሚ ናቸውና ነው፡፡ ይህን ደጋፊ አንጃዎችና ተለጣፊዎች ደግሞ የሕዝብን ጎራ
የካዱ ናቸው፡፡ የፈለጋቸውን ማደናገሪያና የሐሰት ማጠየቂያ ቢደረድሩም ሀቁ ያጋልጣቸዋል፡፡
አንጃ፤ ባንዳ ከሀዲ ይላቸዋል፡፡ የሚሰርቀውን ያጣ ሌባ ሰላማዊ መስሎ ይገባ የተባለውን ደግሞ
ወያኔ አልሰማም ማለት ሞኝነት ነው፡፡

በሐሰት ዜናና በአጉል ተስፋ አንደናገር!